# ASEAC

## የአርሊንግተን የልዩ ትምህርት አማካሪ ኮሚቴ

የአርሊንግተን የልዩ ትምህርት አማካሪ ኮሚቴ (ASEAC) ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተሟልተው ያልቀረቡ ፍላጎቶች ላይ ለመምከር በስቴቱ የሚተዳደርና የትምህርት ቤት ቦርድ የተሾመ ኮሚቴ ነው፡፡

### የ ASEAC ተግባራት ምንድ ናቸው?

- የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የትምህርት ፍላጎቶችን ለ APS ማሳወቅ፡፡
- የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ፍላጎቶች ለማሟላት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን እንዲሁም ስልቶችን በማዘጋጀት ተሳትፎ ማድረግ፡፡
- ወቅታዊ ሪፖርቶችንና ምክሮችን ከትምህርት ቤት ቦርድ ጋር ለመገናኘት ለተቆጣጣሪው እንዲቀርብ ማድረግ፡፡
- ለትምህርት ቤት ቦርድ እንዲቀርብ ከመደረጉ በፊት የልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶችን አቅርቦት ፖሊሲዎችና ሂደቶችን መከለስ፡፡
- ለቨርጂኒያ የትምህርት መምሪያ የ APS አመታዊ እቅድ መከለስ፡፡

### የ ASEAC’s አባላት እነማናቸው?

አባላት ወላጆች፣ የማህበረሰቡ ክፍሎች፣ ተማሪዎችና መምህራን ናቸው፡፡

ASEAC አባላት፡

- በትምህርት ቤቱ ቦርድ እንደ በጎ ፈቃደኛ ማመልከትና መሰየም ይኖርባቸዋል፣
- ቢበዛ ለ 6 አመታት አገልግሎት ይሰጣሉ፣ እና
- ቢያንስ በአንድ ንኡስ ኮሚቴ ውስጥ እንዲያገለግሉ ይበረታታሉ፡፡

### ASEAC እንዴት ሊያግዝዎ ይችላል?

የ ASEAC ወርሃዊ ስብሰባዎች ለህዝብ ክፍት የሆኑና ለአካል ጉዳተኛ ማህበረሰብ ጠቃሚ የሆኑ የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ዳሰሳን ያደርጋሉ፡፡ በእያንዳንዱ ስብሰባ ላይ የህዝብ አስተያየት እድል በመስጠት ማህበረሰቡ ችግሮችን ወደ ASEAC በማቅረብ ትኩረት እንዲያገኙ እድል ይሰጣል፡፡

በስብሰባዎቹ ትኩረትን ያደረጉ ማጠቃለያዎችንና አቀራረቦችን በመለየት፣ በመወያየት እንዲሁም የፍላጎትና የእድገት ቦታዎችን በተመለከተ መረጃን ለመለዋወጥ ያካትታል፡፡

ስብሰባዎቹ ላይ በመሳተፍ እርስዎ፡

- በተማሪ ትምህርት ውስጥ አጋር ለመሆን የሚረዳዎትን መረጃ ያገኛሉ፣
- የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ወላጆችና የትምህርት ባለሙያዎች ጋር ትስስር ይፈጥራሉ፣ እና
- በአርሊንግተን የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን በተመለከተ ፖሊሲውንና የፕሮግራሙን ውሳኔዎችን ለማሳወቅ ያግዝዎታል፡፡

### የህዝብ አስተያየት እንዴት መስጠት እችላለሁ?

ASEAC በእያንዳንዱ ስብሰባ የ 3 ደቂቃ አስተያየቶችን ከህዝቡ ይሰበስባል፡፡ የ ASEAC አባላት ምክሮችን ለማሳወቅና የትምህርት ቤቱን ቦርድ ለመምከር የተወሰዱ አስተያየቶችን ይጠቀሙባቸዋል፡፡

- አስተያየቶች በአካል ወይም በኢሜል ASEAC.mail@gmail.com ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡
- ስብሰባው እንዲጀምር ከመደረጉ ከ 15 ደቂቃች በፊት በእያንዳንዱ የ ASEAC ስብሰባ መግቢያ ላይ የምዝገባ ወረቀት ይለጠፋል፡፡
- አስተያየቶች በግንባር ለሚሰጡ አስተያየቶች በምዝገባ ቅደም ተከተል ይቀበላሉ፡፡
- የህዝብ አስተያየቶች በስብሰባ ቃለጉባኤ ውስጥ የሚካተቱና በ ASEAC ድረገጽ ላይ ይለጠፋሉ፡፡ አስተያየቶች ሲጠየቁ ማንነታቸው ሳይገለጽ ሊቀረጽ የሚችል ሲሆን ነገር ግን የኢሜል አድራሻችን በ FOIA ደንቦች ተገዢ መሆኑን ይወቁ፡፡
- የ ASEACም ሆኑ የAPS ሰራተኞች የህዝብ አስተያየት በቀረበበት ጊዜ ምላሽ ባይሰጡም ነገር ግን ሰራተኞቹ በሚቀጥለው ስብሰባ ምላሽ እንዲሰጡ ይጠየቃሉ፡፡
- የሕዝብ አስተያየት ለመስጠት አስተርጓሚ ወይም ከአካል ጉዳት ጋር የተያያዘ መስተንግዶ የሚያስፈልግ ማንኛውም ግለሰብ ከስብሰባ ቢያንስ 7 የስራ ቀናት በፊት የወላጅ መገልገያ ማእከልን በ 703.228.7239 ወይም prc@apsva.us ማግኘት አለበት፡፡

**ASEAC ስብሰባዎች**

**ሁሉም የ ASEAC ስብሰባዎች ለህዝብ ክፍት ናቸው፡፡**

በመስመር ላይ በመጎብኘት የበለጠ ማወቅ ይችላሉ፡
www.apsva.us/special-education-advisory-committee
ወይም ኢሜል በዚህ ይላኩ፡ ASEAC.mail@gmail.com